# አባይና አድዋ

**ገብረፃድቃን ከበደ** *ሚያዝያ* 7/2003 ዓ.ም

አባይና አድዋ አንድም ሁለትም ናቸው ። አንድ የሚያደርጋቸው በአንድ ዓይነት ፊደል ከመጀመራቸው በላይ በኢትዮጵያ በኢትዮጵያውያን ስሜትና ትኩሳት ዘንድ ሁለቱም ታሪካዊ በመሆናቸው ነው ። የአድዋ ድልና ገድል በኢትዮጵያውያን ሁሌ አዲስ ፣ ጣፋጭ ፣ አንፀባራቂ ሁኖ ይወደሳል ፤ይከበራል ፣ ይሸለላል ፣ ይፎከራል ፣ ይገጠማል ድርሰት ይፃፍበታል ። ይህ የሆነበት ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ ከአጥናፍ አጥናፍ ተሞ የከተተበት ፤ የተዋደቀበት ፤ የውስጥ ቁርሾ ወደ ጎን በመተው የአገር ጉዳይ ከማነኛውም በላይ መሆኑን የተረዱት ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው ነው ።

አፄ ሚኒሊክ ወደ ደቡብ ግዛታቸው ባስፋፉበት ወቅት ከኦሮሞ ህዝቦች ፤ ከደቡብ ህዝቦችና ከጎጃም ህዝብ ቁርሾ ነበራቸው ። ወራሪዎችን አከርካሪውን ሰብሮ በመመለስ የጦርነት ፊተውራሪነታቸውን ያስመሰከሩ የመተማው ሰማእት አፄ ዮሃንስና አፄ ሚኒሊክ በነበረቸው አለመግባባት የትግራይ ህዝብ የበቀል ቂም ሳይዝ ወራሪውን ሃይል በመከላከል ፤ከመሃል አገር የሚመጣውን የአፄ ሚኒሊክ ጦር መንገድ በመምራት ፣ስንቅ በማቀበል ፤ወታደራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ስትራተጅካዊ ቦታዎች በማጥናትና ብስለላ በኩል ከፍተኛ ሚና በመጫወት በአንድነት ወራሪዎችን አሸነፉ ።አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ።ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በቅኝ ግዛት ይማቀቁ ለነበሩ የአፍሪካ አገሮችና የዓለም ህዝቦች ወረሪዎችን ታግሎ ማሸነፍ እንደሚቻል በደማቸውና በአጥንታቸው አስመሰከሩ።ለዚሁ አንፀባራቂ ድል ሁሌም ይወደሳል ፣ይከበራል ፤ይሸለላል ፣ይፎረካል ፣የዓለም ቅርስ ሁኖ ይዘልቃል።

የአባይ ወንዝም በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከአድዋ ድል እኩል ክብደት አለው። የአባይን ወንዝ በተመለከተ ማነው ያላዜመው፣ያልገጠመው፤ያላንጎራጎረው፣ያልዘፈነው ፡ቅኔ ያልተቀኘው? "አረ ስንቱን ስንቱን...." እንደለችው አርቲስት ስለ አባይ ያልተባለ ነገር

የለም።በአጠቃላይ አርቲስት ዜማ ያወጣለትና የዘፈነለት፣ደራሲው ብዕሩን ሰብቆ የገጠመለትና የደረሰለት ፣ፖለቲከኛው በተለያዩ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች ዲስኩር ያሰማለት ቁብ ሳይቆጥር ለዘመናት ፈሰሰ ። ዛሬ ግን የአባይ ወንዝ ''ዕድሜ መስተዋት ነው!!'' ይባል የለ!! ለህዝቦቹ ዳቦና መብራት ሊሆን እጁን የሰጠ ይመስላል።

የዕድሜ ባለጠጎች ሞት አፋፍ ላይ ሁነው ቀወጢው የኑሮ ውድነት ሳይበግራቸው ''አባይን ይገደባል'' የሚለውን የምስራች ዜና በሰሙ ጊዜ ከተጋደሙበት እንደ እምበሶ በመዝለል ''ተመሰገን አምላኬ!! ይህን ቸር ወሬ ያሰማኸኝ።እንግዲህ ያለችኝን የጡረታ አበል ሰጥቻለሁ'' ሲሉ መስማት ከዚህ የበለጠ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ይት ይገኛል?

በእግዚአብሄር ፍቃድ ስትራተጅክ ጠላቶች በደረሰባቸው ቀውስ ምክንያት ቁሞ ቀሮች በሆኑበት ቀውጢ ወቅት የኢትዮጵያ መንግስት በ5 ዓመት የዕደገትና የትራንስፎርሚሽን ዕቅድ የተካተተ ቢሆንም የስትራተጅክ ጠላቶች ሊፈጥሩት የሚችሉት ተፅዕኖ በማጤን '' አባ መላው መንግስት'' ካለፉት ስህተቶች በመማር ''አሁን ነው ጨዋታው '' በማለት '' ታላቁ የሚሌኒየም ግድብ'' በሚል በመሰየም የአባይን ወንዝ በመገደብ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት በማሳየት በውስጥ ዓቅም ለመገንባት የወሰደው ቆራጥ እርምጃ ከውጭ ተፅእኖ በመላቀቅየኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ፣ ወኔ ፣ እልህ ፤ የአገር ፍቅርና ተቆርቋሪነት ግምት ውስጥ በማገባት በ21ኛው በሰለጠነው ክፍለ ዘመን የዚሁ ክፍለ ዘመን ዜጋ እነደቀደምት ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ከዘመን ዘመን የሚሻገር አኩሪ ታሪክ ሰርቶ እንዲልፍ የሚያደርግ ነው። ድንቅ ተግባር!!

የኢትዮጵያ መንግስት ታሪክ ሰሪው ሰፊው ህዝብ ነው ብሎ የሚያምን በመሆኑ እያንዳንዱ ዜጋ '' ሁሉም ቢተባበር .....'' የሚለውን ህብረ ዜማ እንዲያዜም በማድረጉ የኢትዮጵያ ህዝብ ከጫፍ እስከ ጫፍ ቆፎው እንደተነካ ንብ ሰልፍ በመውጣት ለዘመናት ታፍኖ የነበረው ዕምቅ የአበይ ወንዝ ፍቅር ፣ ስስት ፣ጥቅም ላይ ውሎ የማየቱ ጉጉት ሲቃ እየተናነቀው ብፍቅር ደስታውን ሲገልፅ በአንፃሩ ደግሞ ''የእናት ሆድ ዥንጉርጉር'' እንዲሉ ዴሞክራሲ ባለበት አገር እየኖሩ

የዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ባህል ያላዳበሩ የሀገር ነፈዞች ፣ የስትራተጅክ ጠላቶች ነጭ ለባሾች ተቃውሞ አሰሙ። መስከረም ሳይጠባ …. ይባል የለ ጃል !!

መንግስት በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያ የሆነ ሁሉ በሀገሩ ልማት እኩል ተጠቃሚ ተሳታፊ መሆኑን ያምናል። አገር የጋራ መሆንዋን ብጥብቅ ያምናል።የፖለቲካ ልዩነት በየትም ቦታና ጊዜ ሊፈጠር ይችላል ። የአገር ጉዳይ ግን ከዚሁ የጠነከረ ፣ልዩነት በአንድነት የሚገለፅበት መተኪያ የሌለው ነው።ለዚ ነበር መንግስት 'ሁሉም ቢተባበር….' የሚለውን ህብረ ዜማ በማንገብ የአባይን ወንዝ በመገደብ ያለፈው ይብቃን በማለት ለአገር ልማት እንዲውል በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውለደ ኢትዮጵያ ዲያስፖራዎች ለመወያየት አንድ አገራዊ የጋራ አመለካከት እንዲፈጠር ፡ የፖለቲካ ልዩነት እንዳለ ሁኖ ባገር ጉዳይ ተቀራርቦ ተደማምጦ ፣ የፖለቲካ የመቻቻል ባህል እንዲዳብር በማድረግ፤ በዚሁ አጋጣሚ ብሄራዊ እርቅ የሚፈጠርበት አጋጣሚ የሚከሰትበት ታልሞ የቀረበ ነበር።ነገር ግን ተቃዋሚዎች በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ የለም፤ ዕድገት የለም፤የኑሮ ወድነት አይለዋል።ወዘተ የማይሉት የለም።ታደያ ድህነት የሚለውን ቃል ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በተባበረው ክንዳችን ድባቅ እንምታው ሲባል ተቃውሞ ማሰማቱ ፋይዳው ምንድነው? ከዚህ የበለጠ አንድ የሚያደርግ የእናት አገር ጥሪ የት ይገኛል? ወይስ አሜሪካ ካናዳ ሁናችህ የምታሰሙት ዲስኩር የምታነቡት የዓዞ እንባ የውሸት ነበር? ''ሆድ በጎመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ላይ….'' እንደሚባለው ለ19 አመታት ተቃውሞ አሰምታች ውጤት አልባ የሆናችህ ሃቂ ይህናይህ ብቻ ስለሆነ ነው። የአባይ ወንዝ በአገር ወዳድ ሃይሎች ይገደባል !! ትርፉ ትዕዝብት ነው ። የሻዕብያ ጀሌነትና ነጭ ለባሽነት ያወጣል ካለችህ ኢትዮጵያውያን ሳትሆኑ አምቼዎች መሆናችህ ቅጬን ንገሩንና ጆሮኣችን ሌላ ያድምጥ።

ገንዘባችህ ፣ጉልበታችህ ፣እውቀታችህ ለአገር ልማትና ዕድገት የማይውል ከሆነ እቤታችህ መጥቶ ስጡን ብሎ ያሰገደዳችህ ና ያላችህ የለም። ታደያ የኢትዮድያ መንግስት አቋም ለመግለፅ ረጅም መንገድ ተጉዘው የመጡት ጥሪ ከተደረገላቸው ተቃዋሚ ይሁኑ ደጋፊዎች በሰላም ለመወያየት አዳራሽ ሲገቡ ስም እየጠሩ መሳደቡ ፤በአደባባይ አምባጓሮ ማንሳቱ፣የአደጋ ጥሪ ደወል መጫኑ ፣እድል ሳይሰጥ

በመናገርና ግርግር መፍጠር የስለጣኔና የዴምክራሲ መገለጫ ከሆነ ሌላ የዴሞክራሲ ንድፍ ሓሳብ ኣስተምሩን።

ሐሞተ ቢስ የዋሽንግተንና የካናዳ ነውጠኞች ዴሞክራሲ የሚያድገው በአንድ ጀንበር ኣይደለም።ዴሞክራሲ የሚያድገው በሂደት ነው ። አገሮች በዴሞክራሲ የሚየድጉት በኤኮኖሚ ስያድጉ ብቻ ነው ። የኤኮኖሚ ዕድገት በሌለበት ዴሞክራሲ ማስፈን ኣይቻልም ። ህዝቦች ከመንግስት ተፅእኖ ነፃ የሚወጡት ኤኮኖሚያዊ አቅማቸው ስያድግ ብቻ ነው ። ዲስፖራዎች ኢህአዴግን የሚወቅሱት ‘’ የመንግስት ገንዘብ ለፖለቲካ አገልግሎት እያዋለው ነው ።ህዝቡ በገንዘብ ፣ ብስራ ፣በእርዳታ እያለ ቀፍድዶ ይዞታል በማለት ነው’’ የኤኮኖሚ አቅሙ ያልዳበረ ሕ/ሰብ ታድያ ምን ያድርግ? ህዝቡ የተሻለ ኑሮ መኖር ሲጀምርና ከመንግሰት ተፅእኖ ነፃ የሚወጣው ።ህዝቡ ኢህአዴግን ይበቃኛል የሚለው ከኢህአዴግ የተሻለ ለልማትና ለዕድገት ለብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች አኩልነትና አንድነት የሚታገል አማራጭ የፖለቲካ ፓርቲ ስያገኝ ብቻ ነው ። በኤኮኖሚ አድጎና ጎልበቶ ሲወጣ ነው።ለዚሁ መድሃኒት ‘ጨለምተኛ ኣትበሉን ፣ ነጭለ ባሽ አትበሉን ፣ ፅንፈኛ ወዘተ አትበሉን ትለላችህ ። ‘’ ሰንካለ ምክንያት በመፍጠር ሳይሆን ይህንን ተቋቅሞ የህዝብ ሀያልነት አምኖ አገር ውስጥ እንደሚንቀሰቀሱ ተቃዋሚ ሃይሎች የፖለቲካ ልዩነት እንዳለ ሁኖ በአገራዊ ጉዳዮች ተባበሮ መስራት ነው ። መጨረሻ ፍርዱ የህዝብ ይሆናል።ለዚሁ አንዱ ማሳያ በአባይ ወንዝ የሚገነባው ‘’ ታላቁ የሚሌኒየም ግድብ’’ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥሪ ነበር/ ነው። ነገር ግን አልተቀበላችሁትም ፣መንገድ ላይ ረገጣችሁት።

መንግስት ይህንን ጥሪ ሲያደርግ መንገዱ አልጋ በአልጋ ይናሆል ብሎ ወየመ ከደጋፊዎቹ ብቻ ለመወያየት አይደለም ወደ አሜሪካና ካናዳ ልኡካን የላከው ። ውጭ የሚኖሩት ኢትዮጵያውያንን ትውልደ ኢትዮጵያ ሰለአገራቸው በቂ ግንዛቤ አያገኙም ከሚል አንዱ በመረጃ እጥረት ምክንያት ሌላው በተሳሳተ መረጃ ምክንያት በተፈጠረው ክፍተት ቁጥሩ የማይናቅ ዲያስፖራ ለብዙ ዓመታት ያጠራቀመውን ዕውቀት ፤ ልምድና ተሞክሮ ካፒታል ለሃገርና ለወገኑ ጥቅም ሳይሰጥ እስከ ወድያኛውም ይዘውት የሚሄዱ እንዳለሁኖ ኋላ ከመፀፀት ወቅቱ አሁን በመሆኑ

የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲፈጠር በማለት ነበር '' የሆዳን በሆዴን የአንጀቴን ባንጀቴን ልጠይቅሽ.....' እንዳለው አርቲስት ነዋይ ደበበ መንግስት ረጅም መንገድ የተጓዘው።እስከ መቼ በጭፍን ጥላቻ መኖር ይቻላል? እንቀራረብ ፤እንወቃቀስ፣ እንተራረም ሰጥቶ እስከ መቀበል ድረስ እንጓዝ የሚለውን በማንገብ ፤ለመንግስት ያልታየው ችግር በዲያስፖራ እንዲቀርብ ፤በተጨባጭ በአገራችን ያለው የፖለቲካ ፣ የኤኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን እየተመዘገበ ያለው ዕድገት በማብራራት ተቀራረበው ተደማምጠው አንድ የነጠረና የጠራ የጋራ አገራዊ አመለካከት ለመያዝ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለመፍጠር ነበር።ከደጋፊዎቹ ለመወያየት ቢፈልግ ለምን ረጅም መንገድ መጓዝ አስፈለገው? ዘመኑ በፈጠረው ቴክኖሎጂ በኤምባሲውን ቆንሲላ ፅ/ቤቶች በኩል በማሰባሰብ በቪድዮ ኮንፈረንስ ማስተላለፍ አይቀልም ነብር ትላላችህ? ዓላማው ያገር ጉዳይ በመሆኑ ሁሉም በአገሩ ቀናኢ ስለሆነ በአንድነት በድህነትና ሃላ ቀርነት ላይ በቆራጥነት ለመዝመት ነበር።

ሰለዚህ በዋንግተን ዲሲና በካናዳ ስብሰባው እንዲደናቀፍ አድርገናል ብላችህ ''የጀግና '' ጀብድ የሰራችህ የመሰላችህ ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዴ እንዳፈረባችህ ብትሰሙ ። እውነት እነዚህ ኢትዮጵያውያን ናቸው ትላለችህ ? ነው ያለው። አዳዲስ የሰለጠኑ ባንዳዎች ነው የሚለው ።
ስለዚህ ጊዜው ሳይመሽ ንስሃ ግቡና ያስቀየማችሁትን ህዝብ ከጎንህ አለንልህ በሉት።በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ የአድዋ ድል የአባይ ወንዝ መገደብ እኩል ክብደት አላቸው።

ሁሉንም ነገር ወደ ታላቁ የአባይ የሚሌኒየም ግድብ ፕሮጀክት!!